# እንዴት ደህንነቴን መጠበቅ እችላለው?



Amharic

# እንዴት ደህንነቴን መጠበቅ እችላለው?

Amharic
Ethiopia

Copyright © 2025, SIL Ethiopia

http://creativecommons.org/licenses/by-nc-sa/4.0/
You may not use this work for commercial purposes. You may adapt and add to this work, but you may distribute the resulting work only under the same or similar license to this one. You must keep the copyright and credits for authors, illustrators, etc.

Author: Jill Reimer, inspired by a Storyweaver

Translator: Biruktawit Girma
Story,“Awareness of Safety” by Jagruti Rajguru.

“ደህንነቱ የተጠበቀ መሆን ብዙ የተለያየ መልክ አለው! ለምሳሌ፣ አሁን በኮቪድ–19 ወረርሽኝ ወቅት፣ ክትባት መውሰድ አለብን!



አንተም እኔም ክትባቱን ተከትበናል! ክትባቶች ከተለያዩ ህመሞች ይጠብቁናል።”



አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ከተመለሰች በኋላ፣ ሶፋል ከአያቷ ጋር ለማውራት ሮጠች። “አያቴ! አያቴ!" "እንዴት ነው ደህንነታችንን የምንጠብቀው? በላ ጠየቀች። በቀኑ መገባደጃ ላይ ከትምህርት ቤት ስንወጣ መምህሩ ሁልጊዜ ‘ደህና ሁኑ’ ይለናል። ግን ምን ማለት ነው? “ውድ ሶፋል፣ አዎ፣ ደህንነት አስፈላጊ ነው” አለች አያቴ። "ከእኔ ጋር ነይ እና ስለ ጉዳዩ የበለጠ ላስረዳሽ።"

ከዚያም ሀያቴ እንዲህ አለች፤ "አሁን ወደ ኩሽና ወዳለው እቃ ማጠቢያ እንሂድ፤ ደህንነትን ለመጠበቅ ሌላ መንገድ አሳይሻለሁ። ጤናን ለመጠበቅ እጅን በሳሙና እና በውሃ መታጠብ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህን፤ ከመብላትሽ በፊት፣ መታጠቢያ ቤት ከተጠቀምሽ በኋላ እና ምግብ ከማዘጋጀትሽ በፊት ማድረግ አለብሽ።



ሳሙና እና ውሃ በሽታ አምጪ ተህዋሲያንን ያስወግዳሉ። ይህ ጤናሽን ይጠብቅልሻል፤ አለች አያቴ። "ከደህንነት ለመጠበቅ" ሌላ ምን ማድረግ እንችላለን? ብላ ሶፋል ጠየቀች። "ነይ እንይ" በማለት የሶፋል አያት፣ ሶፋልን ወደ ኩሽና ወሰደቻት። “ወደ ማብሰያው እሳት አትቅረቢ፤ እሳቱንም አትንኪ፣ አለበለዚያ ልትቃጠይ ትችያለሽ። በተጨማሪም፣ በምድጃው ላይ የፈላ ውሃ ወይም ዘይት ካለ በጣም ተጠንቀቂ ምክንያቱም በስህተት ከነካሺው በጣም ያቃጥልሻል።



ከዚያም አያቴ፣ “እንዲሁም ለእራት ስጋ ለመቁረጥ የተጠቀምኩበት አይነት ስለታም ነገሮች መጠንቀቅ አለብሽ።” ምክያቱም ስለታም ነገሮች ካልተጠነቀቅን ይቆርጡናል። “ቢላዋውን መጠቀም ትችያለሽ ነገር ግን ራስሽን እንዳትቆርጪ በጥንቃቄ መሆን አለበት።”

ሶፉል “እሺ” አለች፣ “አሁን ክትባት መውሰድ እንዳለብን አውቃለሁ፣ እጃችንን ደጋግመን መታጠብ አለብን፣ በኩሽና ውስጥ ካሉ ስለታማ ነገሮች መጠንቀቅ አለብን... ደህንነታችንን ለመጠበቅ ሌላ ምን እናድርግ?” ብላ ጠየቀች ሶፉል። "ነይ እናያለን" አለች የሶፉል አያት፣ ሶፉልን ከቤት አስወጥታ ወደ ወንዙ ዳርቻ እየወሰደቻት። “ወንዙ አጠገብ ስትሆኚ በጣም መጠንቀቅ አለብሽ” አለች አያቴ። “በዚች ሀገር ብዙ ህጻናት በወንዝ ዳር ሲጫወቱ በአጋጣሚ ወደ ወንዝ ወድቀዋል፣ዋና ስለማያውቁ ደግሞ ሰጥመዋል። ስለዚህ፤ ወደ ወንዙ ውስጥ እንዳትወድቂ በጣም መጠንቀቅ አለብሽ፤ ነገር ግን ዋና ከተማርሽ፤ ውሀ ውስጥ ብትገቢ እንኳን ደህንነትሽን ጠብቀሽ ዋኝተሽ መውጣት ትችያለሽ።”



ሶፋል ቀኝ እጇን ይዛ ጣት በጣት እየጠቆመች፦ "እሺ፡ ክትባቶች፣ እጅን መታጠብ፣ ከእሳት እና ሙቅ ውሃ ወይም እሳት ላይ ከተጣደ ዘይት መጠንቀቅ፣ ስለታማ ነገሮችን መጠንቀቅ፣ መዋኘት መማር! እነዚህን ነው የነገርሽኝ አያቴ!" አለች ሶፋል እጇን ይዛ፤ አምስት ጣቶቿን በመዘርጋቷ አያቷ ሳቀች። "እንዴት ጎበዝ ነሽ ሶፋል! ይህ ለማስታወስ ጥሩ መንገድ ነው። "አሁን እራስሽን ለመጠበቅ የሚረዱሽን ጥቂት ተጨማሪ ነገሮችን እነገርሻለው።"



የሶፋል አያት ሶፋልን ንብረታቸው ከሚገኝበት በአንደኛው በኩል ወዳለው መንገድ ዳር ወሰደቻት። “ሶፋል፣ ይህን መንገድ ስታቋርጪ በጣም መጠንቀቅ አለብሽ” አለቻት። “ቀኑን ሙሉ ወደዚህ መንገድ የሚመጡና የሚሄዱ ብዙ አይነት ተሽከርካሪዎች አሉ። አንዳንድ ጊዜ በጣም በፍጥነት ስለሚሄዱ መቆም አይችሉም። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አሽከርካሪው ትኩረት ስለማይሰጥ ላያይህ ይችላል። ስለዚህ መንገድ ስታቋርጪ መጠንቀቅ የአንቺ ፋንታ ነው።”

ወደ ቤት በመመለስ ላይ እያለን፣ አያቴ፣ “ይኸው ሌላ ልትጠነቀቂ የሚገባ ነገር አለ” አለች እና በመንገዱ ዳር ያለ ተክል እያመለከተች። “የበረሃ ጽጌረዳ ትባላለች። በጣም ቆንጆ ናት፤ ነገር ግን ቅጠሎቿን ከበላሽ በጣም ተታመሚያለሽ! ስለዚህ፤ የትኞቹ ተክሎች ደህና እንደሆኑ እና የትኞቹ ተክሎች መርዛማ እንደሆኑ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው!”



ከዚያም አንድ ትልቅ ቀንድ ያለው የውሃ ጎሽ በመንገዱ ላይ ቀስ እያለ መጣ። እያትየው የሶፋልን ክንድ ይዘው፤ የውሃ ጎሹ እንዲያልፍ ለማድረግ በፍጥነት ወደ መንገድ ላይ ወጡ። አክለውም “ከእንስሳት ተጠንቀቂ፣በተለይም ከዱር እንስሳት እና ከማታውቂያቸው እንግዳ ውሾች” አሏት ።



ሶፋል ግራ እጇን ይዛ ጣት በጣት እየጠቆመች፣ "እሺ ፤ ከትራፊክ፣ ከመርዛማ እፅዋት እና የዱር ወይም እንግዳ እንስሳት ተጠንቀቂ! አያቴ ሌላ ሁለት ልንጨምር እንችላለን?" አያቴ ለአፍታ ካሰበች ቡኃላ። “አዎ ሶፋል።” አለች። ዛፍ ስትወጪ ወይም ከፍ ባለ ወለል ላይ ስትራመጂ እንዳትወድቂ ወይም አጥንትሽ እንዳይሰበር ተጠንቀቂ!" አያቴ ለሌላ ተጨማሪ ጊዜ ካሰበች ቡኃላ፣ “እና፣ ሶፋል – ከአንድ ከማታውቀው ሰው፣ ወይም ከምታውቀው ሰው ጋር ብትሆኚ እና ምቾት ወይም ደህንነት ካለተሰማሽ... ምን ታደርጊያለሽ?” ሶፋል ይህን ለመመለስ ምንም ማሰብ አልነበረባትም። "አያቴ ወደ አንቺ እሮጥ ነበር!" አለች። "እንዴት ደህንነትሽን መጠበቅ እንዳለብሽ አሁን ተረድተሻል ሶፋል?" "አዎ አያቴ!" ከዚያም የሶፋል አያት፣ "አሁን ምሳ እንብላ!" አለች። ሶፋልም “እሺ አያቴ፣ ግን መጀመሪያ እጃችንን መታጠብ አለብን!” አለች።



Let's grow a library
Bloom®